ቀን፡ 13/06/2015 ዓ.ም

የምዝገባ ጥሪ ማስታወቂያ

አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛ መርሃ-ግብር በመጀመሪያ ዲግሪ በ2015 ዓ.ም ለተመደባችሁ ተማሪዎች በሙሉ

ጉዳዩ፡ ወደ ዩኒቨርሲቲ መግቢያ ጊዜ የካቲት 20/2015 ዓ.ም ብቻ መሆኑን ስለማሳወቅ

በቅድሚያ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲን ምርጫችሁ አድርጋችሁ እኛ ጋር ለመማር በመፍቀዳችሁ ታላቅ ኩራት ይሰማናል፡፡ አያይዘንም ወደ ዩኒቨርሲቲ መግቢያ **ቀን የካቲት 20/2015 ዓ.ም ብቻ** መሆኑን አውቃችሁ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ በእለቱ በተመደባችሁበት ህንጻ እንድትገኙ እናሳስባለን፡፡

ዝርዝር አጠቃላይ የምዝገባ እና የገለፃ መርኃ ግብርን የተመለከቱ መረጃዎችን እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው በኩል የሚተላለፉ ሌሎች መረጃዎችን የዩኒቨርሰቲው መገናኛ ዘዴዎችን በመወዳጀት፣ በማጋራትና የደውል ምልክቷን በመጫን ወቅታዊ መረጃዎችን መከታተል ትችላላችሁ፡፡

University Official Website: www.aastu.edu.et

University Official telegram channel፡ https://t.me/pir2011

University Official Facebook Account: https://www.facebook.com/aastu.edu.et

University Official You tube Channel: https://www.youtube.com/channel/UCUpgXuqDCiLfgLPK_FxS-6g

ዝርዝር የምዝገባና የገለፃ መርሃ-ግብር እንዲሁም ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ቅድመ-ሁኔታዎችን ከታች በተመለከተው ሰንጠረዥ ውስጥ መመልከት ይቻላል፡፡

አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሬጂስትራር ጽ/ቤት

ቀን	ዝርዝር ተግባራት	ሰዓት	ፈፃሚ	ቦታ
20/06/2015	ተማሪዎች ዶርሚቶሪ ይረከባሉ	2፡30-6፡30	የክልል ተማሪዎች ድሬደዋን ጨምሮ	ዋናው ግቢ
		7፡00-12፡00	የአዲስ አበባ ተማሪዎች	ዋናው ግቢ

21/06/2015	የትምህርት ክፍሎች ገለፃ (Orientation)	3፡00-6፡30	ID NO፡ ETS0001/15-ETS0500/15	አዲሱ የመመረቂያ አዳራሽ
	የቤተ መከራዎች ጉብኝት (Laboratory Visit)	3፡00-6፡30	ID NO፡ ETS0501/15-ETS1010/15	ዋናው ግቢ
	የትምህርት ክፍሎች ገለፃ (Orientation)	8፡00-10፡30	ID NO፡ ETS1011/15-ETS1520/15	አዲሱ የመመረቂያ አዳራሽ
	የቤተ መከራዎች ጉብኝት (Laboratory Visit)	8፡00-10፡30	ID NO፡ ETS0001/15-ETS0500/15	ዋናው ግቢ
22/06/2015	የትምህርት ክፍሎች ገለፃ (Orientation)	3፡00-6፡30	ID NO፡ ETS0501/15-ETS1010/15	አዲሱ የመመረቂያ አዳራሽ
	የቤተ መከራዎች ጉብኝት (Laboratory Visit)	3፡00-6፡30	ID NO፡ ETS1011/15-ETS1520/15	ዋናው ግቢ
	አጠቃላይ ገለፃ (Orientation)	8፡00-10፡30	ሁሉም አንደኛ አመት ተማሪዎች	አዲሱ የመመረቂያ አዳራሽ
24-25/06/2015	ምዝገባ (Registration)	3:00-10:30	ሁሉም አንደኛ አመት ተማሪዎች	የድሮው መመረቂያ አዳራሽ
27/06/2015	ትምህርት ይጀምራል	በክፍለ ጊዜ	ሁሉም አንደኛ አመት ተማሪዎች	በክፍለ ጊዜ ፕሮግራም

		ፕሮግራም መሰረት		ላይ በተመለከቱ ህንፃዎች እና ክፍሎች

ማሳሰቢያ፡

1. የመኝታ ቤት/የዶርሚቶሪ ህንፃ ቁጥር፣ የመኝታ ቤት/የዶርሚቶሪ ክፍል ቁጥር፣ የዩኒቨርሲቲ ኢሜል አድራስ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲ መለያ ቁጥር (ID No) ከአሁን በፊት ለብሄራዊ ፈተና ስተጠቀሙበት የነበረውን የመ.ቁ (Admission Number) በማስገባት የምታዩበት ማስፈንጠሪያ (ሊንክ) አርብ በ18/06/2015ዓ.ም የሚገለፅ ይሆናል፡፡
2. ወደ ዩኒቨርሲቲ ስትመጡ ብርድልብስ፣ አንሶላ፣ የትራስ ጨርቅ እንዲሁም የስፖርት ትጥቅ ይዛችሁ መምጣት ይጠበቅባችኃል፡፡
3. ለምዝገባ ስትመጡ
   - ✓ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ውጤት ሰርተፊኬት ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ፣
   - ✓ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ትራንስክሪፕት ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ፣
   - ✓ የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ውጤት ሰርተፊኬት ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ፣
   - ✓ አራት 3X4 ፎቶግራፍ እንዲሁም
   - ✓ ሁሉንም ከ21-22/06/2015 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲው የሚሰጥ ገለፃ (Orientation) መከታተላችሁን የሚገልፅ ወረቀት(ገለፃውን ተከታትላችሁ ስትጨርሱ የሚሰጣችሁ ነው) ይዛችሁ መቅረብ ይኖርባችኃል፡፡
4. ሁሉንም ገለፃ መከታተል ግዴታ ሲሆን ያልተከታተለ ተማሪ የማናስተናግድ መሆኑን እንገለፃለን፡፡
5. ከተጠቀሰው ቀን ቀድሞም ይሁን ዘግይቶ የሚመጣ ተማሪን ዩኒቨርሲቲው የማናስተናግድ መሆኑን ከወዲሁ ይገልፃል፡፡

አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሬጂስትራር ጽ/ቤት